በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 174623
ግንቦት 27 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡-ወ/ሮ ኤልሳቤጥ አድማሱ

ተጠሪ ፡- አቶ ገድለጊዮርጊስ አስራት

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትየመ/ቁ 73153 እና 74013 የሆኑ መዛግብትን አጣምሮ በቀን 14/05/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ 212366 በቀን 13/07/2011 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ የጋብቻ ውለን የተመለከተ ሆኖ በስር ፍርድ ቤትየአሁን ተጠሪ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍር ድ አ ፈ ጻ ጸ ም ዓ ላማአ የ ገ ለ ግ ል ም፣

በመ/ቁ 73157 ከሳሽ አመልካችደግሞ ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን በመ/ቁ 74013 የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

ተጠሪ በ24/11/2010 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ንብረት የሆነ በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቀበሌ 15/16 የሚገኝ የቤት ቁጥር 2078 የሆነ ኮንዶሚኒየም ቤትና የቤት ቁሳቁሶች የጋራ ሃብት ይባልልኝ በማለት ክስ መስርተዋል፡፡ በማስረጃነትም የጋብቻ ውልን ጨምሮ ምስክሮችን ዘርዝረዋል፡፡

አመልካች በሰጡት መልስ የቀረበው የጋብቻ ውል በተንኮል ተመስርቶ የተደረገ ነው፤ ከተጠሪ ጋር አብረን አልኖርንም፤ በጋራ ያፈራነውም ንብረት የለም፤ውሉ ይፍረስልኝ አቤቱታ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ በበኩሌ አመልክቻለሁ በመሆኑም በጋራ ያፈሩት ንብረት የለም ይባልልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በመ/ቁ 74013 ባቀረቡት አቤቱታ ግንቦት 06 ቀን 2008 ዓ.ም የፈፀምነው የጋብቻ እና የንብረት ስምምነት ውል የባልና ሚስት ወገን ምስክሮች ያልፈረሙበት በመሆኑ፤ ለህግ ተቃራኒ በመሆኑ፤ በተንኮልና በከባድ ስህተት የተደረገና የውሉ ጉዳይ ሊፈፀም የሚችል ባለመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ ውሉ በሙሉ ፈቃድ እና ስምምነት የተደረገና ሊፈፀም የሚችል በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ይደረግልኝ ብለዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት መዛግብቱን አጣምሮ በመመርመር በሰጠው ውሳኔ ግንቦት 6/2008 ዓ.ም በተደረገው የጋብቻ እና የንብረት ስምምነት ውል ሰነድ ላይ በአመልካች በኩል የቀረቡ ሁለት ምስክሮች ባለመኖራቸው በቤተሰብ ህጉ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 44 መሰረት የጋብቻ ውሉ ፈራሽ ይደረግልኝ ያሉ ቢሆንም በተጠሪ በኩል ፍርድ ቤት በቀረቡት ምስክሮች ቃል እንደተነገረው አመልካች የተጠሪ ጓደኞች የእኔ ምስክር ይሁኑኝ በማለታቸው ስለፈረሙ በውሉ ፎርም ረገድ የቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡ የጋብቻ ውሉ ላይ የጋራ ሃብት ናቸው በማለት ከተገለፁት ንብረቶች መካከል በተጠሪ በኩል የተገለፀውና የቀረበው ቤት የቀበሌ ቤት በመሆኑ የግል ንብረት ባልሆነ ነገር ላይ የተደረገ ውለታ በመሆኑ ፈራሽ ሊሆን ይገባል በሚል አመልካች ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተም በውሉ ላይ ‘ከጋብቻ በፊት የምኖርበት ቤት’ በሚል የተገለፀ በመሆኑና የመንግስት ቤት ቢሆንም

የመጠቀም መብት ጋብቻ በፍቺ በሚፈርስበት ወቅት በመንግስት ቤቶች መመሪያ መሰረት ክፍፍል የሚደረግበት በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም፤ ውሉ የተደረገው በስባድ ስህተት ወይም ተንኮል ስለመሆኑ የቀረበውን ክርክር በተመለከተም የጋብቻና የንብረት ስምምነት የተፈረመው ተጠሪ ቤቱ የግሌ ነው በማለታቸው ምክንያት መሆኑ የተገለፀ ቢሆንም በውሉ የተገለፀው ከጋብቻ በፊት የምኖርበት ቤት በሚል በመሆኑና ተጠሪ ቤቱን የግሌ ነው ብለው በሰሩት ተንኮል ምክንያት የጋብቻና ንብረት ስምምነት የተፈረመ ባለመሆኑ መከራከሪያው ተቀባይነት የለውም። በሌላ በኩል በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ቀበሌ 15/16 ሚኪሊላንድ ህንፃ ቁጥር 53 የቤት ቁጥር 2078 የሆነው የኮንደሚኒየም ቤት በአመልካች ከጋብቻ በፊት የተፈራ ቢሆንም ግራቀኙ ከጋብቻ በፊት ያፈሩት ንብረት የጋራ ሀብት ነው በሚል የጋብቻና ንብረት ስምምነት ውል ያደረጉ በመሆኑ አመልካች የግል ይባልልኝ በሚል ያቀረቡትን መከራከሪያ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም። የቤት ቁሳቁስ መኖሩም አልተረጋገጠም። በአጠቃላይ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ባለሁለት መኝታ ኮንደሚኒየም ቤት የጋራ ንብረት ስለሆነ ከተቻለ በአይነት ካልሆነ በስምምነት በመሸጥ ይህም ካልሆነ በሀራጅ በመሸጥ ይካፈሉ በማለት ወስኗል።

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም የስር ፍ/ቤት ውሳኔንአጽንቷል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው።

አመልካች በቀን30/07/2011 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ በጋብቻ ውሉ ላይ በአመልካች በኩል የቀረበ ሰው የለም፤4ቱም ምስክሮች የተጠሪ ጓደኖች ሲሆኑ ውሉ ከመደረጉ በፊት ጭራሽ አላውቃቸውም፤ ምስክሮችም ከውሉ መደረግ በፊት እንደማያውቁኝ፣ በእኔ በኩል ዘመድ ወይም ጓደኛ እንዳልቀረበ በምስክርነት ቃላቸው አረጋግጠዋል፤ የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 44 በባል ወገን ሁለት በሚስት ወገን ሁለት ምስክር መኖር እንዳለበት በአስገዳጅነት የደነገገበት አላማ የጋብቻ ውሉ ካለው ልዩ ባህሪ አኳያ ነው፤ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ይህን ባለመረዳት የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው። ውሉ የማይንቀሳቀስ ንብረቶቻችንን (ቤቶቻችንን)የባልና ሚስት ጋራ ለማድረግ የተደረገም በመሆኑ የምዝገባ ግዴታ ያላሚላ ነው፤ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የባልና ሚስት የጋራ ማድረግን በተመለከተ የቤተሰብ ህጉ ካላስቀመጠ በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 1677(1)

መሰረት ስለውሎች በጠቅላላ የተደነገገው በሚሚያነት በመተካት መተርጎም አለበት በማለት ያቀረብኩት ክርክር ውድቅ መደረጉም አላግባብ ነው፡፡ በጋብቻ ውሉ የግል የኮንደሚኒየም ቤቱ የጋራ እንዲሆን የተስማማሁት ተጠሪ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 364 የሆነ ባለ አራት ክፍል የግል ቤት እንዳለው በመግለጽ በውሉ ላይም ይህንን ቤት የጋራ ንብረት እንደሆነ በመግለፁ የእኔና የእርሱ የግል ቤቶች ተመጣጣኝ ናቸው በሚል እምነት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ እርሱ የቆጠረልኝ ቤት የቀበሌ (የመንግስት) ቤት መሆኑን ተረድቻለሁ፤ የጋብቻ ውሉ የቀበሌ ቤት የጋራ ሃብት ለማድረግ የተፈፀመ በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል በማለት የፍ/ብ/ህ/ቁ 1705(1) እና 1715 ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ያነሳሁት መከራከሪያም የስር ፍርድ ቤት በውሉ ከጋብቻ በፊት የምኖርበት በሚል የተገለፀ ነው በሚል ከውሉ አንዱን ሀረግ ብቻ በመምዘዝ አጠቃላይ የውሉን ይዘትና መደምደሚያ ሳይመለከት የቀበሌ ቤት በሚል እንደተገለፀ በማስመሰል መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ የጋብቻ ውሉ በግልጽ በግል ያፈሩትን ንብረት የሚል ሲሆን ምስክሮቹም ውሉን ሲፈርሙ ቤቱ የግል ቤት መሆኑን እንጂ የቀበሌ ቤት መሆኑን እንደማያውቁ አስረድተዋል፡፡ በአመልካች በኩል በምስክርነት የቀረቡትና አመልካችና ተጠሪን ያስተዋወቁንና ባልና ሚስት የማገናኘት ስራ የሚሰሩት ግለሰብ ተጠሪን ሲተዋወቋቸው ስማቸውን አቶ በየነ በማለት እንደነበርና ሆኖም የጋብቻ ውሉ ሲፈፀም አቶ ገድለጊዮርጊስ በሚል መፈፀሙና የስም መለዋወጡ ለምን እንደተደረገ ግልጽ እንዳልነበር የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ሲሆን ይህ ሁኔታ የተንኮል ዝግጅት እንደነበር የሚያሳይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የቀበሌ ቤትን የግል ንብረቴ ነው በማለት በአንጡራ ሀብቴ ያፈራሁትን የግል ኮንደሚንየም ቤቴን በወጠነው ተንኮል የጋራ በማድረግ ጋብቻ ይፍረስ በማለት አሸጦ ያለፋበትንና ያልደከመበትን ቤት በጋብቻ አሳቦ ለመካፈል ያደረገው የተንኮልና የማታለል ውል በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ ውሉ እንዲፈርስ ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

ቅሬታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በተጠሪ በኩል በጋብቻ ውሉ ላይ በግል የነበረኝ ..... የምኖርበት ቤት የጋራ አድርጊያለሁ ማለቱቤቱ የቀበሌ መሆን አለመሆኑን አመልካች በወቅቱ ከተረዳችበት አንጻር ነው መመዘን የነበረበት ወይስ የስር ፍ/ቤቶች በመዘኑበት ሁኔታ ነው የሚለውመጣራት ያለበት ነው ተብሎጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን 12/10/2011 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ አመልካች እማኞችን በጠየቀቻቸው መሰረት በተገኙበት ተነቦላት እንደፈረመች ተረጋግጧል፤ የጋብቻ ውሉ የራሷ ድርሻ (ግልባጭ) ለረጅም ግዜ በእጇ እያለ ቅሬታ ሳታቀርብ ቆይታ የአመልካችን ጥፋት ለስር ፍርድ ቤት ካመለከትኩና ኮንደሚኒየም ቤቱ የጋራ ሃብት ይባልልኝ በማለት ክስ ካቀረብኩ በኋላ አመልካች ተታልዬ ነው የፈረምኩት ማለቷ አምናበት እንደቆየችና በመከሰሷ ያነሳችው ሀሳብ መሆኑንበግልጽ የሚያሳይነው፡፡ አመልካች በእድሜም በትምህርትም የበሰለችና ከዚህ ቀደም በትዳር ቆይታ ፍቺ የፈጸመች ከመሆኗ አኳያ የጋብቻና ንብረት ውል ቀርቶ ማንኘውም ውል ሳታምንበትና ሳታጣራ የምትፈርምበት ሁኔታ ላይ አይደለችም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተጠሪ ቤት የመንግስት ቤት ስለመሆኑ የምትረዳበት ብዙ ሂደቶች ነበሩ፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በበቂ ሰነድ እና የሰው ማስረጃ እውነቱን በማረጋገጥ የተሰጠ በመሆኑ ውሳኔው እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከፍሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ግራቀኙ የተገናኙት ባልና ሚስት የማገናኘት ስራ በሚሰሩ ግለሰብ (የአመልካች 1ኛ ምስክር) አማካኝነት ሲሆን አከራካሪውን ግንቦት 6/2008 ዓ.ም የተደረገ "የጋብቻና የንብረት ስምምነት ውል" የተባለ ሰነድ ተፈራርመዋል፡፡ አመልካች የጋብቻ ውሉ የባልና ሚስት ወገን ምስክሮች ያልፈረሙበት በመሆኑ፤ ለህግ ተቃራኒ በመሆኑ፤ በተንኮልና በከባድ ስህተት የተደረገ በመሆኑና ከተጠሪ ጋር አብረን ያልኖርን በመሆኑ ሊፈረስ ይገባል በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ውሉ በሙሉ ፈቃድ እና ስምምነት በአራት ምስክሮች ፊት የተደረገ መሆኑን በማንሳት ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ የጋብቻ ውል ህጋዊ ተግባር ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 42 ስር እንደተደነገገው ተጋቢዎቹ ጋብቻቸው ንብረታቸውን እንዲሁም ግንኙነታቸውን በተመለከተ ስለሚያስከትለው ውጤት በውል መወሰን የሚችሉበት ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓለማአ የገለግልም!

ነገር ግን በዚህ መልኩ ተጋቢዎቹ የሚያደርጓቸው ውሎች አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎችን የሚቃረኑ ሊሆኑ እንደማይችሉ የድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ 3 ያመለክታል፡፡

ከዚህም ሌላ በህጎቻችን "ጋብቻ" በሌሎች ሃገራት እንደሚሆነው ግልጽ ትርጉም የተሰጠው ባይሆንም እንደተቋም የሚወሰድና የጋብቻ ውልም እንደማንኛውም ውል ሁሉ አስገዳጅ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎችን ሊቃረን እንደማይችልና ተቃርኖ ቢገኝ ፈራሽ እንደሚሆን በህጋችን ግልጽ ተመልክቷል፡፡

የጋብቻ ውሉን ፎርም በተመለከተ ውሉ በጽሁፍ ካልተደረገና አራት ምስክሮች ሁለት በባል ወገን ሁለት በሚስት ወገን የፈረሙበት ካልሆነ በስተቀር ውጤት እንደማይኖረው በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 44 ተደንግጓል፡፡ ከድንጋጌው መገንዘብ እንደሚቻለው ውሉ በምስክሮች ፊት እንዲደረግ ያስፈልጋል ብቻ ሳይሆን ምስክሮቹ ከሁለቱም ወገን የተውጣጡ እንዲሆኑ የግድ ይላል፡፡ ይህም የግራቀኙን ጥቅም በሚያስከብር መልኩ ከተንኮልና ማታለል በፀዳ ሁኔታ ተገቢው ድርድር ተደርጎበት ስምምነት ላይ የተደረሰበት መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ስለሆነም በአንድ ወገን የቀረቡ አራት ምስክሮች በመኖራቸው ግራቀኙን በአግባቡ የማያውቁ እና ጥቅማቸውን በእኩል የማያስከብሩ ከሆኑ ቁጥራቸው አራት የሆኑ ምስክሮች ስለፈረሙበት ብቻ የጋብቻ ውሉ የህጉን ፎርም ጠብቆ የተደረገ ነው ሊባል አይችልም፡፡ ከፍሲል እንደተገለፀው ህጉ አራት ምስክሮች ሁለት በባል ወገን ሁለት በሚስት ወገን የፈረሙበት ካልሆነ በስተቀር ውጤት አይኖረውም በማለት መደንገጉም ዓላማው ምስክሮቹ እንደሌላው ውል አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ተዋዋዮቹ ውሉን ተስማምተው የፈፀሙ መሆናቸውንና የውሉ ቃል ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ጋብቻ ካለው ልዩ ባህሪ አኳያ የሁለቱም ወገኖች ተገኝተው ተጋቢዎቹ መብትና ጥቅማቸው በሚዛናዊነት እንዲጠበቅ ለማድረግም ነው፡፡

ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ አራት ጓደኞች ብቻ በተገኙበት ግራቀኙ ውሉን ማድረጋቸው በስር ፍርድ ቤት በተረጋገጠበት ሁኔታ በውሉ ፎርም ረገድ የቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም በማለት የተደረሰበት መደምደሚያ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 44 የተደነገገውን አስገዳጅ የውል ፎርም ይዘት መሰረት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነ ድለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸ ምዓለማአ የገለግልም!

ያደረገ ባለመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው። ውሉ በህጉ አግባብ ሁለት በባል ወገን ሁለት በሚስት ወገን የፈረሙበት ባለመሆኑ ውጤት የለውም ብለናል።

የጋብቻ ውሉ በፎርም ምክንያት ውጤት አይኖረውም ከተባለ ደግሞ ተንኮልና ማጭበርበር የተፈፀመበት ነው እንዲሁም በማይቻልና በማይፈፀም ጉዳይ ላይ የተደረገ በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል በሚል የቀረበውን ክርክር መመርመርና ውሳኔ መስጠቱ አስፈላጊ ስለማይሆን ተከታዩን ወስነንል።

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመ/ቁ 73153 እና 74013 የሆኑ መዛግብትን አጣምሮ በቀን 14/05/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ 212366 በቀን 13/07/2011 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል።

2. በአመልካችና ተጠሪ መካከል ግንቦት 6/2008 ዓ.ም "የጋብቻና የንብረት ስምምነት ውል" በሚል የተደረገው የጋብቻ ውል በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 44 በተደነገገው የውል ፎርም መሰረት ሁለት በባል ወገን ሁለት በሚስት ወገን የፈረሙበት ባለመሆኑ ውጤት አይኖረውም ብለናል።

3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ን